# እንኳን ለ35ኛው የኢሕአፓ የምሥረታ በዓል በደህና አደረሰን
# ኢሕአፓ - ጽናት - ኢሕአፓ

ኢሕአፓ በሚያዝያ 1964 ዓ.ም. በወጣት ኢትዮጵያውያን ሀገር ወዳድ የተመሠረተ ሲሆን የምስረታውም ሆነ የቀራጥ ትግሉ ዋና መነሻው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማድረስ ነበር። ድርጅቱ ሲመሠረት በዚህ መስክ ስሬ ተመክሮና ቅርስ ስላልነበረውም በሂደትና በትግሉ እሳት እየተፈተነ ተመክሮ መገብየት የግድ ነበር። ኢሕአፓና አባላቱም በዚሁ ትግል ወቅት በደርግ አስከፊ ቀይ ሽብር ተዳርገው በገጠር ደግሞ በጠባቡ ወያኔም ተጠቅተው ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ኢሕአፓ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. የፖለቲካ ፕሮግራሙን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ በማስተካከልና በማሻሻል የሕዝብ አለኝታነቱን አረጋግጦና እራሱንም ለመጪው ፍልሚያ አዘጋጅቶ ህልውናውን አሳወቀ።

ኢሕአፓ ከሕዝቡ ውስጥ ተወልዶ፤ ከሕዝቡ ጋር እየተጓዘ፤ ከሕዝቡ ጋር እየታገለ፤ ኃይልና መከታውን ሕዝብ ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ ነው። ኢሕአፓ ጥንካሬው፤ ሀብቱ፤ መሣሪያው፤ ልሣኑ፤ ድፍረቱ፤ ሕይወቱ ወዘተ. ከሕዝብ ጋር በመሆኑ ነው ከኢትዮጵያ ሕዝብ አዕምሮ ሊፋቅ ያልቻለው። ኢሕአፓ መሠረቱን የገነባው በሕዝብ ላይ ነው ስንል በአርሶ አደሩ፤ በላብ አደሩ፤ በሠራተኛው ክፍል፤ በሥራ አጡ፤ በምሁሩ፤ በወጣቱ፤ በተማሪው፤ በሴቶች፤ በወታደሩ፤ በአዛውንት እናት አባቶች፤ በታዳጊ ሕፃናት ከመሆኑም በተጨማሪ ዘር ሳይለይ፤ ሃይማኖት ሳይገድበው፤ የዕድሜ ሳይወስን፤ ክልል ሳይገድብ፤ የተንቀሳቀሰ ብቸኛ ፓርቲ ነበር። ነውም።

የኢሕአፓ መሥራች አባላትና ከተመሠረተ ጀምሮ ድርጅቱን በመቀላቀል የታገለና እየታገለም ያለው ኢትዮጵያዊ ያለ ጥርጥር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ፍቅር በፖለቲካ ዓላማው፤ ለዚህ ዓላማ መሳካት ባደረገው ትግልና በከፈለው መስዋዕትነት የገለጠና እየገለጠም ያለ የዚያ አኩሪ ትውልድ እምብርት የሆነ ክፍል ነው።

ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነው። ኢሕአፓ ዓላማው ዓላማችን ነው። ኢሕአፓ የሕዝብ ፓርቲ ነው። ኢሕአፓ የሕዝብ ቤት ነው። ኢሕአፓ ቤተ-ዲሞክራሲ ነው። ስንል ሕዝባዊነቱን ለማጉላትና በድርጅቱ ውስጥ ያለውን መብትና ነፃነት ለማስገንዘብ ነው። ኢሕአፓ የመንግሥት ፖለቲካ ሥልጣን ባይዝም በቃኝ፤ ታከተኝ፤ ሰለቸኝ ሳይል ለአለፉት 35 ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመብት ባለቤትነትና የበላይነት ታግሏል። አታግሏል። አያሌ መስዋዕትነት ከፍሏል። አሁንም ይህንን እየተገበረ ይገኛል። ኢሕአፓ በትግል ተመክሮው የኢትዮጵያ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ትንታኔ ከመስጠት ባሻገር እንደየወቅቱና እንደተለዋዋጩ የዓለም ፖለቲካ ሁኔታ፤ የሀገሪቷንም በማጣመር በየጊዜው የፖለቲካ ፕሮግራሙን ቢያሻሽለም በመነሻ ዓላማውንና አቋሙ ግን እንደጸና እውን ነው። ይህም ጽናቱ ነው ሁሌም በአባላቱና በሕዝቡ ውስጥ ኩራት ሆኖ ያለው። ለሕዝባቸው ነጻነትና ለፓርቲያችን ህልውና የተሰውት አባልቱንና ደጋፊዎቹን አርማ በጽናት ይዞ መጓዙ ነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ኢሕአፓ መሠረቱ ሊናጋ ያልቻለው።

"መሬት ለአራሹ"፤ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት"፤ "የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ" ወዘተ. መሪ መፈክሩ አድርጎ ከፋሽስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ ገና ከጅምሩ ኢሕአፓ ተናንቋል። በዚህም የትግል ወቅት ከመሀል ከተማ እስከ ዳር ገጠሩ በመንቀሳቀስና አንኳር አስኳሉን በሕዝቡ ውስጥ በመትከል ከባድ መስዋዕትነት የከፈለ ፓርቲ ነው። ፋሽስታዊው ደርግ ለሥልጣኑ መራዘምና ለፈላጭ ቆራጭ አገዛዙ መረጋጋት ከሕዝብ ጋር አጣብቂኝ በገባበት በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ የመጨረሻውን የጭካኔ እርምጃ በመውሰዱ በሀገሪቷ ላይ አጠቃላይ የጅምላ አፈና፤ እስርና ግድያ በማስፈን

የኢትዮጵያ ሕዝብና ልጆቹን ሊገለጽ በማይቻል ሁኔታ በመጭፍጨፍ የኢሕአፓን ውጥረት በመገላገል በሕዝቡ ላይ እንደአሻው ተንሰራፍቶና ረግጦ ለተወሰነ 10ተ ዓመታት ሊቆይ ችሏል።

ኢሕአፓ በወቀቱ የገነባውን የበላይነት በትግል ስልት አካሄድ ከተነጠቀና ትግሉ ከተኮላሸ በዋላ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ትልቅ ሀዘንና ፀፀትን ፈጥሯል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ሞቱ፤ እናት፡ አባት ተሰቃዩ፡ ሕፃናት ስነልቦናዊ ጥቃት ደረሰባቸው፤ በሀገሪቷ የሙታን መንደር ተበራከተ። ሕዝባችን የሌለበት ፍርሃት፤ መሸበር፤ በራስ አለመተማመን አዙሪት ውስጥ ተዋጠ። ገባ። ሀገር በመላ በሃዘን ማዕበል ውስጥ ተዘፈቀች። ደርግና ሎሌዎቹ ቦረቁ፤ በሕዝብ ደም ሐሴት አደረጉ; ሻፓኝ ከፈቱ፤ የምሥራች ተለዋወጡ፤ "ምታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ብቻ ሳይሆን ወደ ደምሳሽነት ተሸጋገረ" ብለው ፎከሩ። በዚህም በሕዝብና በልጇ ደም የገዥነት ዕድሜአቸውን ለጊዜውም ቢሆን አራዘሙ።

ኢሕአፓ ከ1970ዎቹ በተለይ በአዲስ አበባና በከተሞች የነበረው እንቅስቃሴ ከተኮላሸ በኋላ በገጠሩ እንቅስቃሴውን ቀጠለበት። ሆኖም በወያኔና ሻቢያ ተጨማሪ ሴራ በገጠሩም ከፍተኛ መስዋዕትነት ሊከፍል ተገዷል። ወያኔም አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ወቅት አንስቶ ዋናው ጠላቱን ኢሕአፓን በማድረግ በሚንቀሳቀስበት ሁሉ በማነፍነፍ በድጋሚ ከባድ ጉዳት በድርጅቱ ላይ ማድረሱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በዚህ ሁሉ የተባበረ የጠላት ምት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የማጥቃት ዘመቻ ኢሕአፓ ተመቷል። ተሰውቷል። አሁንም ሆነ ወደፊት የሕዝብ ጥያቄ እስካልተሟላ ድረስ ምን ጊዜም በሕዝብ ላይ የሚደርስ ጥቃት፤ ሰቆቃ፤ ምት ማለት የኢሕአፓ ነውና መስዋዕትነት ከመክፈል ወደኋላ አላለም። አይልምም። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ቤተ-ሕዝብ ነው የምንለው። ኢሕአፓ የምላዕተ ሕዝቡ ነው የምንለው።

በዚህ የ35 ዓመታት የሕዝብና የኢሕአፓ የነፃነት፤ የመብትና ዲሞክራሲ ትግል ውስጥ ሕዝብን ሳይክዱ፤ ለፓርቲውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባላቸው ጽናት በየቦታው የተሰዉትን የኢሕአፓና የሕዝብ ልጆች ዓርማ ይዘው ትግሉንና ፓርቲውን እዚህ ለአደረሱት፤ ደከመኝ፤ ሰለቸኝ ሳይሉ ቤታቸው ኢሕአፓ፤ ልጃቸው ኢሕአፓ፤ ትዳራቸው ኢሕአፓ፤ ሥራቸው ኢሕአፓ፤ ሕይወታቸው ኢሕአፓ ላደረጉት አባላቱ ለአኩሪ ጽናታቸውና ታሪካቸው ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። ኢሕአፓ እንደ ሕዝባዊነቱ፤ አሁንም እንደጥንቱ በህዝቡ ውስጥ ሆኖ ከሕዝቡ ጋር ትግሉን ለመጋራት፤ በተለይ አሁን በምንገኝበት ወሳኝ የትግል ወቅት፤ በተገኘው የሀገሪቷ ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ በመነሳት ምን መደረግ አለበት? ምን ማድረግ አለብን? ጠንካራ ጎናችን የቱ ነው? ደካማውስ? ወዘተ. የሚሉትን በጥሞናና በቅንነት በመመርመር የኢሕአፓ 35ኛው የምሥረታ አከባበር ለቀጣይ ትግሉ ጽናቱን በማደስ የትግል አርማው የሚውለበለብበት፡ ሰማዕታት የሚዘከሩበት ከዋለኛው የመጨው የሚታቀድበት በዓል ይሆን ዘንድ ምኞታችን ነው።

ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር ለመፍታት አለን ብለው እንደ አደይ አበባ ወቅት ጠብቀው ፈክተው እንደሚረግፉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሳይሆን ለሚደረገው የአርነት ትግል ሁሌም አደይ አበባ ነው። ጥንትም፡ አሁንም፡ ወደፊትም የነፃነት ድል በሕዝብ እስኪታጀብ ድረስ እየተዋደቀ ያለ፡ ትግሉ መቆራረጥ የሌለው፡ እንቅስቃሴው በቀጠሮ የማይጓዝ፡ ቀን ተሌት ስለ ሀገርና ሕዝብ አጀንዳ የሚውለበለበበት መድረክና የሕዝብ ድርጅት ነው።

ኢሕአፓ በ35 ዓመት የትግል ተመክሮው ከስህተት የፀዳ ነበር፡ ነውም ብሎ መናገር ራሱን የቻለ ስህተት ነው። ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ያለው ራዕይና ጽናት እንደተጠበቀ በሂደት ላይ ስህተት ተሰርቷል። ይህ ደግሞ ምንጊዜም የሚነሳና በስህተትነቱ የታመነበት ለትምህርት ሰጪነቱ በታሪክ መዝገብ የሚሰፍርና የሚቀበለው እንደሆነ ጥርጣሬ አይገባንም።

ኢሕአፓን የራሱ ስህተቶችና ድክመቶች ካደረሱበት ችግሮች ሌላ የወታደራዊው ደርግና ተባባሪ ቡድኖች የተቀነባበረ ሽብርና ጭፍጨፋ፥ የአካባቢና የሌሎች ሀገሮች ፀረ-ኢትዮጵያ አቀዋሞችና እንቅስቃሴዎች፥ እንዲሁም የጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶች ሻጥርና ተደጋጋሚ ጦርነቶች፥ እስካሁንም ያልቆሙ የማጥፋት ሙከራዎች ያለጥርጥር ጎድተውታል። መላልሰው አዳክመውታል። ይሁን እንጂ ኢሕአፓ ስንል ሁሌም ባመነበት ጸንቶ ሳይፈራና ሳይንበረከክ ሁሉንም አምባገነን ኢ-ዲምክራሲያዊ ኃይል እየተፋለመ የቆየና እየተፋለመ ያለ፥ ለፀረ-ኢትዮጵያ ባዳ ኃይሎችም ያላደረ፥ ሀገራዊ፥ ኅብረ ብሄራዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ፥ ለመሠረታዊ ለውጥ፥ ለፍትህና ርትዕ፥ ለእኩልነትና ለአንድነት፥ ለእድገትና ልማት፥ በጽናት የቆመ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

ኢሕአፓ በትግል ሂደት ውስጥ ያፈራቸው አባላቱ በሚያምኑበት ዓላማ ጽኑዎች፥ መንፈሰ ጠንካራዎች፥ ንቁና አይበገሬዎች በመሆናቸው፥ የትግል ጉዞው ረጅምና መራራ ቢሆንም ማንም ኃይል ሊያጠፋው ያልቻለ፥ ሊያጠፋውም የማይችል በእርግጥም በሕዝብ ፍቅር የተጠናከረና የማይበገር ድርጅት ነው። ለዚህም ነው ኢሕአፓና ጽናት - ጽናትና ኢሕአፓ የተያያዙ ናቸው የሚባለው።

ኢሕአፓ ስንል በቆራጥነት፤ በታማኝነት ለሕዝብ መብትና ነፃነት ያደረገውን ተጋድሎ በማሰብ ነው። በሕዝቡ ውስጥ ተጠንስሦ በሕዝቡ ውስጥ እንደአበበ ሁሉ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታነቱን አጉልቶ ለፖለቲካ ስልጣንና ለገዲብ አልባ ዲሞክራሲ መስፈን የሚታገል ፓርቲ ነው። ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርና ሕዝብ እስካሉ ድረስ ኢሕአፓም አለ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ፤ ግርፋት፤ እስራት፤ ግድያ ሲበዛ የኢሕአፓም ይበዛል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲመቱት ኢሕአፓን ያመዋል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወጥቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና መብት ተሟጋች ኃይል እንደመሆኑ ኢሕአፓን ማጥፋት ማለት ሕዝብን ለማጥፋት ከመሞከር የማይተናነስ ዕልምና ቅዥት ነው። ኢሕአፓ በትግል ሂደቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተራበ፤ ተጠማ፤ ተሰቃየ፤ ታሰረ፤ ተሰደደ፤ መስዋዕትነት ከፈለ እንጂ ከቶም አልከሰመም። አይከስምምም።

ኢሕአፓ 35ኛውን የምሥረታ በዓሉን ሲያከብር በትግሉ የተሰውበትን አባላቱን እየዘከረ፥ የት እንደደረሱ ደብዛቸው የጠፋውን እያሰበ፥ በአካላዊ ሰውነት ጉዳት የደረሰባቸውንና የስነልቦናዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑትን እያበረታታ አሁንም "ፍጹም ነው እምነቴ፤ ለትግሉ ነው ሕይወቴን" እየዘመረ ነው። በዓሉ ለአለፉት ዓመታት ምን ሰራን? በተለይ ከ34ኛው የምሥረታ በዓል ማግሰት ምን አቅደን ምን ያህሉ ስኬታማ ሆነ? በውጥን የቀሩትስ ምክንያታቸው ምንድን ነው? አዎንታዊ ጐናችን የቱ ነው? ደካማውስ? ወዘተ. ታይተውና ተገምግመው ለቀጣዩ 36ኛ ዓመት ምን ይዘን መቅረብ አለብን? ዕቅዳችን ምን መሆን አለበት? ካለፈው ዓመት ከአገኘነው ትምህርት ለሚቀጥለው ምን መተግበር አለብን? ይህ ነው የኢሕአፓ 35ኛ ዓመት ክብረ በዓል ሻፓኝና ርችት። የሕዝብ አጀንዳ። የትግል አጀንዳ።

ሀገራችንና ሕዝባችን ከተደቀነባቸው አስከፊ አደጋ ለማላቀቅ፥ የሕዝቡን የሥልጣን የበላይነት ለማረጋገጥ የትግላችን አካሄድ ምን መሆን አለበት? ተብሎ የሚታቀድበት ኃይሉንና አይበገሬ አባላቱን አጠናክሮ ከደጀኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በወያኔና በጠላቶቻችን መቃብር ላይ 36ኛውን የፓርቲውን ምሥረታ በዓል በሀገራችን ምድር ላይ እናከብረው ዘንድ ለመራራው ትግል ዳግም ዝጉጁነት፥ ዳግም ጽናት የሚታደስበት ክብረ በዓል። 35ኛው የኢሕአፓ የምሥረታ በዓል።

ኢ.ሕአፓ

- ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ሕላዌ
- በሕዝቧ እኩልነት ላይ ለተመሠረተ አንድነት
- ለሕዝቧ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭነት
- ለሰባዊ መብት መከበር
- ለመድበለ ፓርቲ ድሞክራሲ መስፈን
- ለሕዝብ አንድነት የሚመች ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ለመመሥረት
- አርሶ አደሮችን የመሬትና የመብታቸው ባለቤት ለማድረግ
- መንግሥታዊ ተሳትፎ የተወሰነበት የገበያ ኢኮኖሚ ለማስፋፋትና ለማጠንከር
- ለማህበራዊ ፍትህ
- ለፈጣን ልማትና ዕድገት
- ለዘላቂና አስተማማኝ ሰላም
- ለማኅበራዊ (ሶሻል) ዴሞክራሲ

ትላንትም ታግሏል ዛሬም ይታገላል።

ኢ.ሕአፓ ዛሬም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፏል።
ኢ.ሕአፓ ዛሬም ለመስዋዕትነት ዝግጁነቱን ይገልጣል።
ኢ.ሕአፓ አሁንም እንሰባሰብ፣ እንደራጅ ይላል።
ኢ.ሕአፓ ኢትዮጵያን ከጥፋት አድነን የሕዝቡን መብትና ክብር በትግል እናረጋግጥ ይላል።
ኢ.ሕአፓ ሁሉም ዜጋ፣ ሁሉም ሀገር ወዳድ፣ ሁሉም ለመብቱ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊ የበኩሉን ተሳትፎ ያድርግ ይላል።

ኢትዮጵያ ዛሬም ሆነ ወደፊት ለሀገራቸውና ለወገናቸው በጽናት በቆሙ፣ መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ በሆኑ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!!!

35ኛውን የኢ.ሕአፓ ምሥረታ ምክንያት በማድረግ።          ሐምሌ 01/1999 ዓ.ም.